የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-03.5/15/28
ቀን 11/04/2015

ለተከበሩ አቶ አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

ለክብርት ወ/ሮ ሂክመት አብደላ

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ዋና ዳይሬክተር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 11 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 10 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 21 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ጌታሁን ደምሴ
የፋይናንስና ኮሜርሺያል መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ /2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን የዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የ2014 የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በቦርዱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡

ምንም እንኳን ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸውና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1. በተለያዩ ጊዜያት ለተሰጡ ስልጠናዎች የተረደጉ የመስተንግዶ ወጪዎችን በተመለከተ፤

ሀምሌ 2009 ዓ/ም ገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የወጪ ቅነሳ መመሪያ ተራ ቁ. 7 በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በአግባቡ በመፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ እንደሚያስፈልግ እና በተቻለ መጠን ስብሰባዎች በየተቋማቱ የመሰብሰቢያ አዳራሾች በማካሄድ ለሆቴሎች የሚወጣውን ወጪ ማስቀረት እንደሚቻል እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቁ. በጠ1/6/2 በቀን 18/12/2010 የወጪ ቅነሳ መመሪያው ቀጣይነት ያለው መሆኑን በመገንዘብ የመ/ቤቱ የበላይ አመራር ጥብቅ በሆነ ዲሲፕሊን የወጪ ቁጠባ መመሪያ ተግባራዊ እንደሚደረግ ማሳወቁን ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት በመ/ቤቱ የተከናወኑ ስብሰባዎች እና ስልጠናዎች የወጪ ቅነሳ መመሪያን በተከተለ መልኩ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በመ/ቤቱ ውስጥ ሶስት ትንንሽ አዳራሾች ማለትም ከ15-18 ተሳታፊ ሊይዙ የሚችሉ መኖራቸውን እንዲሁም ቦርዱ በኪራይ በሚገኝበት ህንፃ 5ኛ ወለል (Floor) ላይ የሚገኘውን የመሰብሰቢያ አዳራሽ የወለለ ስፋት 260 ካ.ሜ የሆነው ከ300-400 ተሳታፊ መያዝ የሚችል ከቤት ክራይ በተጨማሪ በወር ብር 6,000.00 (ስድስት ሺህ) እየተከፈለበት ያለ በሚፈልጉበት ሰአት በወር 2 ቀን መጠቀም የሚችሉ መሆኑን የቤት ክራይ ውላቸው ላይ ቢገልጸም ለቦርዱ ሰራተኞች ከተደረጉ የተለያዩ ስብሰባዎች እና ስልጠናዎች ውስጥ ፡-
- በቀን 30/05/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 2220 ብር 926,119.07 በሶስት ዙር ብዛታቸው 30 ፣21 እና 30 በተለያዩ ቀን ለተሳተፉ ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ቀን በአዳማ ከተማ በተካሄደው በእቅድ ዝግጅት (ቢ.ኤስ.ሲ)፣ ካሰኬድ እና በሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የመስተንግዶ አገልግሎት የተከፈለ፤
- በቀን 02/10/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 2492 ብር 291,448.35 ብዘታቸው 70 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች ለአንድ ቀን በአዳማ ከተማ ለተካሄደው

የውስጥ አሰራር ማኑዋልን ፤ የውጭ ተገልጋዮች የእርካታ ዳሰሳ ጥናትን ፤ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት እና የቡድን ስራን በተመለከተ ከሰራተኛ ጋር የተደረገ ውይይት የመስተንግዶ አገልግሎት ለኤግዚኪዩቲቭ ሆቴል የተከፈለ፤

- በቀን 23/10/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 2578 ብር 23,799.76 ብዛታቸው 14 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች ለአንድ ቀን በአዲስ አበባ በተካሄደው ለኦዲት ጥራት እና ቁጥጥር ፣ የፋይናንሽያል ሪፖርት ግምገማ እና ክትትል ባለሙያዎች የስነ-ምግባር ስልጠና የመስተንግዶ አገልግሎት ለኢሊሊ ሆቴል የተከፈለ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ለቦርዱ ሰራተኞች የተሰጡ የተለያዩ ስልጠናዎች፣ ስብሰባዎች ወይም ግንዛቤ ማስጨበጫዎች በተቻለ መጠን የቦርዱን የመሰብሰቢያ አዳራሾች በመጠቀም ለሆቴሎች የሚወጣውን ወጪ ማስቀረት ሲቻል በድምሩ ብር 1,241,367.18 የሆቴል የመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፤

2. <u>ለሶስተኛ ወገን እንዲዘጋጅ የተሰጠ የቦርዱ የአምስት ዓመት (ከ2013 እስከ 2017) ስትራቴጂክ እቅድን በተመለከተ</u>፤

ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/1/59/14 በቀን 8/03/2013 በጻፈው ደብዳቤ የቦርዱ ዋና ዋና ግቦችና አመላካቾችን የያዘ እንዲሁም ግቦቹ በመሳካታቸው የሚገኙ ጥቅሞችን የሚመለከት የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ (2013-2022) ተዘጋጅቶ እና የአምስት ዓመት እቅድ እንዲላክ ያሳሰበ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ቦርዱ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ (ከ2013-2017 ዓ.ም) በራሱ የሰው ሃይል በተውጣጡ ባለሙያዎች እቅዱን መስራት ለምን እንዳልተቻለ እና በሶስተኛ ወገን እንዲሰራ የተወሰነበት የስራ አመራሩም ሆነ የዳሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ወይም ሌላ የአማራጭ ሃሳብ ባልቀረበበት ሁኔታ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን የውስን ጨረታ ግዥውን በማስፈቀድ አሸናፊ ከሆነው የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት የቦርዱን የአምስት ዓመት እቅድ በቀን 03/09/2014 ዓ.ም በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 2426 ብር 533,724.46 ክፍያ በመፈፀም እንዲያዘጋጅ የተደረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት በተመለከተ

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ቦርዱ የ2014 የበጀት ዓመት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ለየፕሮግራሞቹ ከተደለደለው የመደበኛ በጀት ሂሳብ በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሙ በተመለከቱት አንዳንድ የወጪ አርዕስቶች ከ10% በላይ ሲታይ፦

በበጀት ዓመቱ ለቦርዱ ከተደለደለው መደበኛ በጀት በድምሩ ብር 6,026,609.44 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ፤

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

1. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 2 ንብረት አመዘጋገብና አስተዳደር ፤አንቀጽ 3 የስቶክ አስተዳደር እንዲሁም አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም ፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሰረት የቦርዱ የንብረት አያያዝ ፣ አጠቃቀም እና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፦

- የቋሚ ፤ አላቂ ፤ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች ዕቃዎችን በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ እና በባለፈው ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይ የቀረበ እና ተገቢውን ማስተካከያ ያልተደረገበት መሆኑ፤
- አዳዲስ የፕሪንተር ቶነር model 80/81A ብዛት 25 ፣ የፕሪተር ቶነር model C-EXV40 ብዛት 16 ፤ ላፕቶፕ HP ኮምፒውተር ብዛት 13 ፤ ወረቀት መጠረዣ ማሽን ብዛት 1 ፣ ፋክስ ማሽን mode L/150 ብዛት 1 ከ2011 በጀት ዓመት ጀምሮ በንብረት ክፍል ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ ፤
- ያገለገሉ ብዛታቸው 10 የሚሆኑ ኤል ሼፕ ጠረጴዛዎች ተጠግነው አገልግሎት እንደሚሰጡ እና እንዳማይሰጡ ሳይለዩ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ በንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ ፤

- ብዛታቸው 12 የሚሆኑ ያገለገሉ ፕሪንተሮች ተጠግነው ለስራ ይውላሉ ተብለው ከአንድ አመት በላይ በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ፤
- ብዛታቸው 71 የሆኑ ተመላሽ ላፕቶፖች ፤መጠረዣ ማሽን ብዛት አንድ ከአንድ አመት በላይ ያለአገልግሎት በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
- የተወሰኑ አላቂ ዕቃዎች A4 የስራ ወረቀቶች ፣ መጽሐፍት፣ ከመሬት ከፍታ ሳይኖረው እቃዎቹ ለብልሽት በሚዳረጉበት ሁኔታ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

2. <u>የሪፖርት እና የሂሳብ መግለጫ አቅራቢ አካላት ምዝገባን በተመለከተ፤</u>

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሰራሩን መወሰኛ የሚኒስተሮች ደንብ ቁጥር 332/2007ዓ.ም አንቀጽ 16 ቦርዱ የባለሙያዎችን ስምና ሌሎች ዘርዝር መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች የያዘ መዝገብ ይይዛል፤ ይጠብቃል ወቅታዊ ያደርጋል፡፡ የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት እና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር ኢሂኦቦ 804/2013 አንቀጽ 8/1/3 ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ተገቢውን ክፍያ በመክፈል አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት ፤ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ቦርዱ በሚወስነው የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴ በመጠቀም ለቦርዱ ማቅረብ እና መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ከደንበኞችና የባለድርሻ አካለት ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶሬት በተሰጠን ማስረጃ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በቦርዱ በሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት የተመዘገቡ ድርጅቶች ጠቅላላ ብዛት ኤሌክትሮኒክስ የሪፖርት አቅራቢዎች ምዝገባ ስርዓት (Reporting Entity Registration Data base) እየተመዘገበ ሲስተሙ በ2011 በጀት ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች በመቋረጡ በማንዋል ሲሰራ የነበረና የካቲት 2014 ዓ.ም አዲስ ዳታ ቤዝ ለምቶና የነበረው አሰራር ተሻሽሎ ምዝገባ ቢጀመርም የቀድሞ የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት የህዝብ ጥቅም ያለበት ምድብ የተመዘገቡ በመሆኑ በአዲሱ መመሪያ መለያ መስፈርቱ በመቀየሩና ወደ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች የሚካተቱ በመሆኑ ቀድሞ በዳታ ቤዝ የተመዘገበው እና በማንዋል ሲስተሙ ተቋርጦ በነበረበት ወቅት የተመዘገበው በትክክል ተጣርቶ አዲስ ተሻሽሎ በተዘጋጀው

ኤሌክትሮኒክስ የሪፖርት አቅራቢዎች ምዝገባ ስርዓት (Reporting Entity Registration Data base) ሙሉ መረጃው ባለመግባቱ በቦርዱ በፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሰረት አጠቃላይ በሂሳብ ሪፖርት አቅራቢነት የተመዘገቡ ድርጅቶች በቁጥር ብዛት 21,848 እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎች ያቀረቡ ድርጅቶች ጠቅላላ በቁጥር ብዛት 844 መሆኑን የሚያሳይ መረጃ ቢኖርም የጠራና ትክክለኛ መረጃ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑ፤

- የሂሳብ አቅራቢ አካለት በቁጥር ደረጃ በቦርዱ መጥተው የተመዘገቡትን ብቻ እንጂ በሃገር ደረጃ ምን ያህል እንደሆኑ የማይታወቁ እና የተደራሽ ውስንነት ያለበት መሆኑ፤
- በሂሳብ ሪፖርት አቅራቢነት የተመዘገቡ እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርቶችን ያቀረቡ ድርጅቶች ፋይል በዳይሬክቶሬት ውስጥ ቢያዝም ሃላፊነት ተሰጥቶት ፋይሎቹን በድንብ አደራጅቶ የሚይዝ ፤ የሚጠብቅ ሲጠየቅም የሚሰጥ ባለሙያ ያልተመደበለት መሆኑ ፤
- በአራት የተለያዩ ክፍሎች ፋይሎቹ የሚገኙ ሆነው በአንደኛ ክፍል በሂሳብ ሪፖርት አቅራቢነት የተመዘገቡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሂሳብ መግለጫዎች ያቀረቡ ድርጅቶች በሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት ማለትም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ሆኖ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS) ፣ መካከልኛና አነስተኛ ድርጅት ሆነው ለአነስተኛና መካከለኛ በወጣው በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS for SME) እና የሲቪል ማህበረሰብ እና የበጎ አድራጎት ድርጅት በአለም አቀፍ የፐብሊክ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎች (IPSAS) እና በቢዝነስ አይነታቸው በትክክል ተለይተውና ተደራጅተው ያልተቀመጡና አቀማመጣቸውም በመደርደሪያ ላይ ሳይሆን በመሬት ላይ ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ የተቀመጡ መሆኑ ፤
- በሶስተኛው ክፍል የተቀመጡ ፋይሎች ደግሞ በቀድሞ የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት መሰረት የግለሰብ ድርጅት እና ህብረት ሽርክና ሆነው በመካከለኛ እና አነስተኛ የሪፖርት አቀራቢ ምድብ ተመዝግበው የነበሩና በአዲሱ መመሪያ መለያ መስፈርቱ (Threshold) በመቀየሩ የተነሳ

በሪፖርት አቅራቢነት የማይቀጥሉና የሚወገዱ በሚል ውሳኔ ሳይሰጥባቸው ተከማችተው ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- በአራተኛ ክፍል ደግሞ ከጥቂት ፋይሎች በስተቀር ምንም ፋይል የሌለበት መሆኑ፤

3. <u>የፋይናንሻል ሪፖርት ግምገማን በተመለከተ፤</u>

የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006ዓ.ም አንቀጽ 24/1 ቦርዱ የቀረበለትን የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርቶች ይህንን አዋጅ ጠብቀው የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሂሳብ መግለጫዎችን እና ሪፖርቶቹን ሊመረምር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት በፋይናንስ ሪፖርት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በተሰጠን መግለጫ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከደንበኞችና የባለድርሻ አካላት ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶሬት በተሰጠን መረጃ መሰረት የፋይናንሻል ሪፖርት ያቀረቡ አካላት በሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት ማለትም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ሆኖ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS) ብዛት በቁጥር 634 ፣ መካከለኛና አነስተኛ ድርጅት ሆነው ለአነስተኛና መካከለኛ በወጣው በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS for SME) ብዛት በቁጥር 42 እና የሲቪል ማህበረሰብ እና የበጎ አድራጎት ድርጅት በአለም አቀፍ የፐብሊክ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎች (IPSAS) ብዛት በቁጥር 168 በአጠቃላይ ብዛት በቁጥር 844 የፋይናንሻል ሪፖርት ያቀረቡ ድርጅቶች መኖራቸውን የሚያሳይ መረጃ ቢኖርም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ሆኖ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS) ብዛት በቁጥር 634 ውስጥ በፋይናንስ ሪፖርት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በተሰጠን መረጃ መሰረት 12 የፋይናሽል ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሂሳብ መግለጫዎች ተገምግመው ወደ ሪቪው ፓናል የተላለፉ ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስት የፋይናሽል ሪፖርት አቅራቢ አካላት ያቀረቡት ሂሳብ መግለጫዎች በግምገማው መሰረት ግብረ-መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ በሂደት ላይ መሆኑን ቢገልጽም የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ሆኖ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS) ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ያደረጉ የፋናንሻል ሪፖርት አቅራቢ አካላት(ድርጅቶች) ግምገማው በሂደት ላይ በመሆኑ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ ፤

- ቦርዱ የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል ሆኖ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS) መሰረት ፋይናሽል ሪፖርት እንዲገመገም ቅደሚያ ተሰጥቶት እንዲሰራ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ እና ክትትል ማኑዋል (Financial Reporting and Monitoring Manual) በማውጣት የግምገማ ሂደት ላይ መሆኑ ቢታወቅም በመካከለኛና አነስተኛ ድርጅት ሆነው ለአነስተኛና መካከለኛ በወጣው በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS for SME) እና የሲቪል ማህበረሰብ እና የበጎ አድራጎት ድርጅት በአለም አቀፍ የፐብሊክ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎች (IPSAS) የፋይናንሻል ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ምንም አይነት ግምገማ ያልተደረገባቸው እና ለግምገማው የሚያግዙ የአሰራር ማንዋሎች ያልወጡላቸው መሆኑ ፤

በድምሩ ብዛት በቁጥር 844 የፋይናንሻል ሪፖርት አቅራቢ በቦርዱ መኖራቸው ቢገለጽም ከገምጋሚው ክፍል ባለሙያዎች ብዛት (የቦርዱ ስድስት ባለሙያዎች ፣ በዋናነት በኮንትራት ተቀጥሮ የሚሰራ አንድ አማካሪ ባለሙያ እንዲሁም ማንዋሎችን በማውጣት እንዲሁም ግምገማውን በማገዝ በACCA የሙያ ማህበር በኩል በኮንትራክት የተቀጠሩ አማካሪዎች ጋር ሲነፃፀር ተመጣጣኝና በሚፈለገው ልክ ግምገማውን ለማድረግ በቂ ናቸው ለማለት የማያስችል መሆኑ፤

4. <u>በቦርዱ ፍቃድ የተሰጣቸው የሂሳብና የኦዲት ድርጅቶችን ፋይል አያያዝን በተመለከተ</u>፤

ኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሰራሩን መወሰኛ የሚኒስተሮች ደንብ ቁጥር 332/2007ዓ.ም አንቀጽ 16 ቦርዱ የባለሙያዎችን ስምና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች የያዘ መዝገብ ይይዛል ፤ ይጠብቃል ወቅታዊ እንደሚያደርግ ይደነግጋል፡፡ ቦርዱ በድንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት እየተወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤-

ከሙያ ትምህርትና የብቃት ማረጋገጫ ፈተናዎች ዳይሬክቶሬት ፈቃድ የተሰጣቸው የሂሳብ እና የኦዲት ባለሙያ ወይም ድርጅቶች መረጃ በE-Service የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ምዝገባው ቢከናወንም ሲስተሙ ምዝገባ ብቻ እንጂ ምን ያህል የሂሳብ እና የኦዲት ድርጅቶች ፈቃድ እንደተሰጣቸው የተጠቃለለ ሪፖርት (Summary Report) የማያወጣ መሆኑ፤

5. <u>የግዥ ሰነዶች አያያዝን በተመለከተ፤</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻፀም መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀፅ 6/23 የግዥ ክፍል ሃላፊነትና ተግባር አንዱ የግዥ ሰነዶችን መያዝ ፤ መጠበቅና ፤ ከሚመለከታቸው ህጋዊ አካል ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ግዥ ክፍሉ ለሂሳብ ማወራረጃነት የግዥ ሰነዶችን ለፋይናንስ ክፍል ቢልክም ከግዥ ጋር ተያዥነት ያላቸው ሰነዶች ለምሳሌ የጨረታ ሰነድ ፣ ውሎች ፣ ቃለ-ጉባኤዎች የመሳሰሉትንና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታሰቡትን የግዥ ሰነዶችን በክፍሉ ውስጥ በደንብ አደራጅቶ ያልያዘ መሆኑ፤

ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻፀም መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀፅ 6/23 የግዥ ክፍል ሃላፊነትና ተግባር አንዱ የግዥ ሰነዶችን መያዝ ፤ መጠበቅና ፤ ከሚመለከታቸው ህጋዊ አካል ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ግዥ ክፍሉ ለሂሳብ ማወራረጃነት የግዥ ሰነዶችን ለፋይናንስ ክፍል ቢልክም ከግዥ ጋር ተያዥነት ያላቸው ሰነዶች ለምሳሌ የጨረታ ሰነድ ፣ ውሎች ፣ ቃለ-ጉባኤዎች የመሳሰሉትንና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታሰቡትን የግዥ ሰነዶችን በክፍሉ ውስጥ በደንብ አደራጅቶ ያልያዘ መሆኑ፤

6. <u>የፋይናንስ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም ክፍል አምስት አንቀጽ 27 እና 28 የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ፋይናንስ መዛግብት ቢያንስ ለ10 ዓመት ማቆየት እንዲሁም ወንጀል የተፈጸመባቸው ሰነዶች በፍርድ ቤት ውሳኔ እስኪያገኙ ድረስ መቆየት እንዳለባቸው ፣ የፋይናንስ መዛግብቶቻቸውንም ፣ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ሰነዶች እና የፋይናንስ መጻጻፍ የተደረገባቸው ሰነዶች ማለትም ልዩ ልዩ የሂሳብ ሪፖርቶች ፣ ሌሎች የፋይናንስ መግለጫዎች ፣ የግዥና የክፍያ ሰነዶች፣ የገቢ ደረሰኞች ፣ የክፍያና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ሰነዶችና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ፣ የፋይናንስ መጻጻፍ የተደረገባቸው ሰነዶች እና ሌሎች የፋይናንስ ግንኙነት የተደረገባቸው ሰነዶች እስኪወገዱ ድረስ በቂ ጥበቃ ተደርጎላቸው ሊቀመጡ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ቦርዱ ፡-

የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶች አጠባበቅ ባለቤትነት ተሰጥቶት መያዝ ያለበት ሰነድ ያዥ ያልተመደበ በመሆኑ የሂሳብ ሰነዶቹ የሂሳብ ሰራተኞች ምዝገባ አከናውነው ሲጨርሱ

ሰነዶቹን በሰነድ ማረካከቢያ ቬርቫል ወይም ሞዴል 42 ተመዝግበውና ርክክብ ተደርጎላቸው በአግባቡ በቂ ጥበቃ ተደርጎላቸዋል ያልተቀመጡ መሆኑ፤

<u>የህግ ጉዳዮችን በተመለከተ፡</u>

1. <u>የዋጋ ማቅረቢያ ግዥን በተመለከተ</u>፤

የእቃ ግዥ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሲፈፀም በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር ወይም የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ሳያረጋግጥ እንዲሁም በግዥ ክፍሉ በሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ማወዳደሪያ ሰንጠረዥ እና ቃለ-ጉባኤ ላይ የፋይናንሻል ግምገማ እንጂ የቅድመ ግምገማ ሰነዶች ወይም የሕጋዊነት ብቃት ማስረጃዎች በትክክል ማቅረባቸው ሳይረጋገጥ ወይም ሳይገመገም በኦዲት ናሙና ከታዩት ውስጥ በድምሩ ብር 1,298,354.83 በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ መፈጸሙ፤ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት